## ‹‹የጳውሎስ ኦን ላይን ቅኔ ቤት ድኀረ ገጽ››

### ስለ መምህሩ ዐጭር ታሪክ

1. **የዜማ ቤት ትምህርት**

ወላጆቼ እድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ ታኅሣሥ 17/1983 ዓ.ም በምዕራብ ጎጃም ደምበጫ ከተማ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከሚገኙት የድጓ ሊቅ ከሆኑት ሊቀ ጠበብት ውዱ ፈረደ ወስደው አደራ ሰጡኝ ። ሊቀ ጠበብት መምህር ውዱ ፈረደም በአደራነት ተቀብለው ያስተምሩኝ ዘንድ ጀመሩ ።

በዚህ ትምህርት ቤት የአጎቴ ልጅ አንማው ዐየነው የድጓ ተማሪ ስለነበር የራሱን ትምህርት ማለትም ድጓውን በአትሮንሱ ከፊቱ ዘርግቶ ከመምህሩ እየተማረ እኔን ደግሞ ከጎኑ ቁጭ አርጎ እየተቆጣጠረ ያስተምረኝ ነበር ። በመምህር አንማው ቁጥጥር ምክንያት ሌሎች ተማሪዎች በሦስት ዓመት ቆይታ የተማሩትን የፊደል ፣ የአርባዕቱ ወንጌል ንባብ እና የመዝሙረ ዳዊት ትምህርት እኔ በዐሥር ወራት ጨርሼ ቀድሚያቸው ወደሚቀጥለው የጾመ ድጓ ትምህርት ተሸጋገርኩ ። ከሦስት ዓመት የዜማ ትምህርት ቆይታ በኋላ መስከረም 1986 ዓ.ም ወደ ቅኔ ቤት ሄድኩ ።

2. **ቅኔ ቤት ትምህርት**

**ሀ. ጎጃም**

☞ **ደብረ ምጥማቅ**

ለመጀመሪያ ጊዜ የቅኔ ትምህርት የጀመርኩት በምዕራብ ጎጃም ደምበጫ ከተማ አስተዳደር ሥር በሚገኘው ከደምበጫ ወደ ፈረስ ቤት በሚያስኬደው መንገድ ከደምበጫ ከተማ ከፍ ብሎ ካለው የሰቀለ ማርያም ተራራ እንዳለቀ የምትገኘው 'ደብረ ምጥማቅ' ተብላ በምትጠራው ቦታ ከሚገኙት መምህር ይትባረክ ቅኔ ተማርኩ ።

☞ **ጫፍቃት ማርያም**

'ጫፍቃት ማርያም' ተብላ በምትጠራው ቦታ ከሚገኙት መምህር ለይኩን ቅኔ ተማርኩ

☞ **ዋድ ኢየሱስ**

ዋድ ኢየሱስ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከደምበጫ ከተማ ወደ የዘለቃ በሚያስኬደው የመኪና መንገድ ከየጎመዲ ቀጥሎ መርካቶ ሥላሴ ሳይደርስ የሚገኝ አገር ነው ። በዚህ ቦታ የቅኔ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ የነበሩት "መሪጌታ ተከሥተ ብርሃን" ይባሉ ነበር ። ከርሳቸው ቅኔን ተምሬያለኹ ።

☞ **ሉማሜ ማርያም**

ሉማሜ ማርያም በምሥራቅ ጎጃም ዞን ከደብረ ማርቆስ ወደ ደጀን ሲከድ ከአምበር (አነደድ ወረዳ) ቀጥሎ የሚገኝ ወረዳ ነው ። በዚህ ቦታ የቅኔ ጉባኤ ዘርግተው የሚያስተምህሩት መሪጌታ መክብብ ደሴ ይባላሉ ። ከርሳቸው ቅኔን ተምሬያለኹ ።

☞ **ደጀን ጊዮርጊስ**

ደጀን ጊዮርጊስ በምሥራቅ ጎጃም ዞን ከደብረ ማርቆስ ወደ አዲስ አበባ ሲከድ ከወጀል ቀጥሎ የሚገኝ ወረዳ ነው ። ከደጀን በኋላ የዐባይ በርሃ ነው ። ከጎጃምና ከጎንደር ተነስተው ወደ አዲስ አበባ ሲሄዱ እና ከአዲስ አበባ ወደ ጎጃም ሲሄዱ መንገደኞች ያርፉባታል ። በዚህ ቦታ የቅኔ ጉባኤ ዘርግተው የሚያስተምህሩት መሪጌታ መርሐ ጽድቅ (ናቄ) ይባላሉ ። ከርሳቸው ቅኔን ተምሬያለኹ

☞ **አማኑኤል**

አማኑኤል በምሥራቅ ጎጃም ዞን ከደብረ ማርቆስ ወደ ባሕር ዳር ሲከድ  የሚገኝ የማቻክል ወረዳ ዋና ከተማ ነው ። በዚህ ቦታ የቅኔ ጉባኤ ተክለው የሚያስተምሩት መሪጌታ አክሊሉ ይባላሉ ።

☞ **ጨጎዴ ሀና**

ጨጎዴ ሀና በምዕራብ ጎጃም በቋሪት ወረዳ ሥር የሚገኝ ሲሆን ከሰከላ ወረዳ ወደ አዴት ወረዳ በሚያስኬደው መንገድ ከልጃምበራ መድኀኔ ዓለም እና ከአርብ ገቢያ መካከል እና ከትልቁ ተራራ አዳማ ሥር ይገኛል ። የጨጎዴው መምህር ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው የቅኔዩን አሰካክና ቅንብር የቅኔ አነጋገር አይተው አደነቁ ። በጉባኤው እንድጸና እና ፍሬያማ እንድሆን ይመክሩኝ ነበር ። እኔም  ትምርቴን በሚገባ ተከታትየ የቅኔ አስነጋሪና ዘራፊ በመሆን ለቅኔ መምህርነት

የሚያስፈልገውን ኹሉ በመቀጸል "ብቁ የቅኔ መምህር" ኾኘ በ12/1994 ዓ.ም የቅኔ የምስክር ማስረጃ ተቀበልኩ ።

**የመምህርነት ጊዜ**

ተምህርቴን ጨርሼ ወደ ትውልድ ሥፍራዬ በመመለስ በምዕራብ ጎጃም ዞን ደምበጫ ከተማ በሚገኘው ጽርሐ አርያም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የካቲት 12/1994 ዓ.ም ተማሪዎችን ይዤ ሄድኩ ። በአንድ ቀን ሠላሳ ሁለት ጎጆዎች ሠርተን በርካታ ተማሪዎችን ማስተናገድ ችለናል ። የተማሪዎች ቁጥር ግን ገደብ በሌለው ሁኔታ እየጨመረ መጣ የጎጆዎች ብዛትም ከመቶ ሃምሣ በላይ ሲሆን የተማሪዎች ቁጥር 6 የቅኔ ዘራፊና አስነጋሪ ፣ 32 ዋና የቅኔ አስቀጻዮች ፣ 50 ንዑሳን አስቀጻዮች እና ሌሎች 271 ተራ ተማሪዎች በጥቅሉ ከሦስት መቶ በላይ ደቀ መዛሙርት ነበሩ ።

**ለ. አዲስ አበባ**

☞ ***የመጀመሪያ ዲግሪ***

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሆነው ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲ በማታ (Extension) የግእዝ ቋንቋ ለመማር ወሰኘ መስከረም 2011 ዓ.ም በመጀመሪያ ዲግሪ ተመዘገብኩ ። በዚህ ዩኒቨርሲቲ በርካታ የቅኔ መምህራን በመኖራቸው ያለኝን ዕውቀት ለማዳበር ቅኔ በመንገር ከሊቀ ሊቃውንት መምህር ገብረ ሕይወት ፈንታሁን ቅኔ ሞልቼ ቅኔ በማስነገር ወይም በማስተማር አግዛቸው ነበር ።

☞ ***የኹለተኛ ዲግሪ***

ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲ በመጀመሪያ ዲግሪ ሰኔ 25/2014 ዓ.ም ከተመረቅኹ በኋላ በቀጣዩ ዓመት መስከረም 2015 ዓ.ም በግእዝ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ በመደበኛው መርሐ ግብር /Regular/ የኹለተኛ ዲግሪ ጀመርኩ ። በዚህም ዶክተር ዘላለም መሠረት የሚባሉ የቅኔ መምህር አጠቃላይ ስለግእዝ ቋንቋ በዘመናዊ የአጠናን ዘዴ አስተምረውኛል ። እኔም ትምህርቴን በአግባቡ ተከታትዩ በመጨረስ አራት ነጥብ (4.00) በማስመዝገብ የመመረቂያ የጥናት ጽሑፍ ውጤትም ‹‹እጅግ በጣም ጥሩ›› በሚል ሰኔ 29/2016 ዓ.ም በከፍተኛ ማዕረግ ተመርቂያለኹ ። በመቀጠልም

በዚኹ ዩኒቨርሲቲ ለመምህርነት ተመድቤ ከመስከረም 2017 ዓ.ም ጀምሮ በግእዝ ቋንቋቀና ሥነ ጽሑፍ እያስተማርኩ እገኛለኹ ።

## የዘመናዊ ትምህርት ቆይታ

☞ **የመጀመሪያ ደረጃ እና የኹለተኛ ደረጃ ትምህርት**

በምዕራብ ጓጃም ዞን ደምበጫ ከተማ በሚገኘው ቹኔር የመጀመሪያ ደረጃ ዘመናዊ ትምህርት ቤት መስከረም 5/1996 ዓ.ም አንደኛ ክፍል ተመዘገብኩ ። በ2000 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቴን አጠናቅቄ በዚሁ በደምበጫ ከተማ በሚገኘው የደምበጫ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት መስከረም 2001 ዓ.ም ዘጠኝኛ ክፍል ገባሁ ። በዚህም ትምህርት ቤት በ2002 ዓ.ም የማትሪክ ፈተና ወስጄ 3.56 ነጥብ በማምጣት ወደ መሰናዶ (ፕሪፓራቶሪ) መስከረም 2003 ዓ.ም የማኅበራዊ ትምህርት ዘርፍ በመምረጥ አስራ አንደኛ ክፍል ገባሁ ። በመጨረሻም አገር አቀፍ የመግቢያ ፈተና /Entrance Exam/ በመፈተን የመሰናዶ ትምህርቴን 2004 ዓ.ም አጠናቅቄ አጠቃላይ ድምር 393 ነጥብ በማምጣት በ2005 ዓ.ም ወደ ሐረማያ ዩኒቨርስቲ ተቀላቀልኩ ።

☞ **የዩኒቨርሲቲ ትምህርት**

መስከረም 27/2005 ዓ.ም ዓለማያ /ሐረማያ/ ዩኒቨርስቲ ገባሁ ። ከዚህ ዩኒቨርስቲ ትምህርቴን ከመቸውም ጊዜ በላይ ጠንክሬ በመከታተል ሰኔ 25/2007 ዓ.ም በመጀመሪያ ዲግሪ 3.70 ነጥብ በማስመዝገብ በከፍተኛ ማዕረግ ተመረቅኹ ። በመቀጠልም በአዲስ አበባ በሚገኘው ያርድስቲክ ኢንተርናሽናል የትምህርት ተቋም በ2012 ዓ.ም የሁለተኛ ዲግሪ (ማስተርስ) ትምህርት ጀምሬ ነሐሴ 23/2013 ዓ.ም 3.82 ነጥብ በማምጣት በ"እጅግ ከፍተኛ ማዕረግ" ተመረቅሁ ። አኹን በአዲስ አበባ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በባለሙያነት እየሰራሁ እገኛለሁ ።

## በዚኽ ድኅረ ገጽ የሚሰጡ ትምህርቶች

### ፩. ንባብ

**የንባብ ምንነት ፡-** ንባብ "አንበበ ፣አነበበ" ከሚለው ግስ የተገኘ ሲኾን በጽሑፍ የሠፈረን መልእክት ማነብነብ ፣መናገር ፣ ሆሄያትን መጥራት ፣ መቍጠር ፣ወዘተ የሚል ትርጕም ይሰጣል ። አለቃ ኪዳነ ወልድም "ንባብ በቍሙ ፤ ነገር ፣ ቃል ፣ ጩኸት" (መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ፣ ገጽ ፮፻፲፱) በማለት ይፈቱታል ።

**በሌላ አገላለጽ ፡-** ንባብ ማለት ከአንድ የተጻፈ ነገር ላይ መሠረታዊ የኾነውን ሐሳብ መረዳት ፣ ነጥሎ ማውጣት ፣ የጸሓፊውን መልእክት መገንዘብ ፣ወዘተ እንደኾነ የቋንቋ ምሁራን ያስረዳሉ ። **ሥርዐተ ንባብ ፡-** በማንኛውም ቋንቋ የአነባበብ ሥርዐት አለ ። በአነባበብ ሥርዐትም የተነሣ በድምፅም ፣ በቃላትም ፣ በመዋቅርም ወዘተ ተመሣሣይ ከኾኑ አደረጃጀቶች (መዋቅሮች) የተለያዩ መልእክቶችን እናገኛለን ።

የአነባበብ ሥርዐታችንን ባለማስተካከላችን በርካታ የትርጕም ችግሮች ይፈጠራሉ ። ይኽ እንደ ማንኛውም ቋንቋ ሲኾን በግእዝ ቋንቋ ደግሞ እጅግ ትኩረት የሚያሻው ነው ። ለምሳሌ ቀደሳ በተነሽና በወዳቂ ሲነበብ የሚሰጠው ትርጕም የተለያየ ነው ። ምሳሌ ፡- **ቀደሳ** ወአክበራ እምኵሎን መዋዕል ሲል "ቀደሳ" በአነባበብ ሥርዐቱ ወድቆ ይነበብና ትርጕሙም ከዕለታት ኹሉ ለይቶ አከበራት የሚል ይኾናል ። ውእቶን አንስት **ቀደሳ** ፈጣሪሆን ሲል ደግሞ "ቀደሳ" በአነባበብ ሥርዐቱ ተነሥቶ ይነበብና ትርጕሙም እነዚያ ሴቶች ፈጣሪያቸውን አመሰገኑ የሚል ይኾናል ።

## ክፍላተ ንባባት

**ዐበይት ንባባት ፡-** የሚባሉት አራት ሲኾኑ እነሱም ተነሽ ፣ ተጣይ ፣ ሰያፍ እና ወዳቂ ናቸው ። **ንኡሳን ንባባት ፡-** ተናባቢ ፣ ኢተናባቢ ፣ ጠብቀው የሚነበቡ ፣ ላልተው የሚነበቡ ፣ በጥቅል የሚነበቡ ፣ በመቍጠር የሚነበቡ ወዘተ ናቸው ።

## የንባብ ትምህርቶች

- የዘወትር ጸሎት
- ውዳሴ ማርያም
- አንቀጸ ብርሃን
- ይዌድስዋ መላእክት
- መልክዐ ማርያም
- መልክዐ ኢየሱስ
- መልክዐ ሚካኤል
- የወንጌል ንባብ
- መዝሙረ ዳዊት
- የግብረ ሐዋርያት ንባብ ወዘተ ናቸው ።

## ፪. የግእዝ ቋንቋ

የግእዝ ቋንቋ ታሪክና ጠቀሜታ ግእዝ በአፍሪካ ቀንድ በኢትዮጵያና በኤርትራ በጥንት የተመሠረተና ሲያገለግል የቆየ ቋንቋ ነው ። ግእዝ በኢትዮጵያ መንግሥት መደበኛ ቋንቋ ነበር ። ግእዝ እስከ ፲ኛው ክፍለ-ዘመን መጀመሪያ ድረስ ዋነኛ የመግባቢያ ቋንቋና ልሳነ ንጉሥ ነበር ። ከ ፲፫ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ግን ሙሉ በሙሉ መነገር አቁሞ በሰሜን ኢትዮጵያ በትግርኛ እንዲኹም በማእከላዊው ክፍል ደግሞ በዐማርኛ ተተካ ። ዛሬ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ይሰማል ። በሰሜን ኤርትራ የሚገኘው ትግረ የሚባል ቋንቋ ከኹላቸው የሰሜን ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ለግእዝ በቅርብ ይዛመዳል ። ትግረ ፸ በመቶ ግእዝ ነውና በመቀጠል ትግርኛ እና ዐማርኛ ናቸው ።

ጳውሎስ ኦንላይን ቅኔ ቤት ከሚሰጣቸው ትምህርቶች አንዱ የግእዝ ቋንቋ ነው ። የግእዝን ቋንቋ ከፊደል ትርጉም ጀምሮ ግእዝን አቀላጥፎ እስከ መናገር ፤ በግእዝ ማንበብና መጻፍ ፤ በግእዝ የተጻፉ መጻሕፍትን እስከ መተርጐም ድረስ ለማስተማር አቅዶ እየሠራ ነው ።

### ግእዝ ቋንቋ ትምህርቶች

- ☞ ከፊደላት ትርጉም ጀምሮ
- ☞ ነጠላ ግስና ርባታ
- ☞ ነባር ስም ቃላት
- ☞ አንቀጽና የአንቀጽ አይነቶች
- ☞ ገቢርና ተገብሮ
- ☞ ቅጽልና የቅጽል አይነቶች
- ☞ የዋህና መሠሪ ርባታ
- ☞ የንባባት ትርጕምና ርባታ
- ☞ የግእዝ ዐውዳዊ ፍች
- ☞ ከግእዝ ወደ ዐማርኛ መተርጐም
- ☞ ከዐማርኛ ወደ ግእዝ መተርጐም

## ፫. ቅኔ

ለመኾኑ ቅኔ ለምን ይጠቅማል?

የቅኔ ጥቅሞች ለፍልስፍናና ጥበብ ድንቅ የኾነ ምርምር ለመሥራት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ለሀገር ፣ ለሕክምናና ለቋንቋዎች ጥናት ፣ ለማኅበራዊ ጥናት እና ለታሪክ ፣ ለሥነ ጽሑፍ እና ለሥነ ግጥም ፣ ለተውኔት እና ለመጻሕፍት ጥናት የግእዝ ቋንቋን ለማወቅ ፣ በግእዝ የተጻፉ መጻሕፍትን ለመተርጐም ፤ በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ ንባባትን ቃላትን ፣ አገባቦችን ፣ ግሦችን ፣ የንባብ ስልቶችን ጠብቆ ለማንበብና ለመረዳት ።

### የቅኔ የትምህርት ኺደት

#### ሀ. የመምህሩ ድርሻ

ግስ መግሰስ/ማውረድ ፣

ታሪክ መተረክ/የወር ታሪክ ፣የዓመት ታሪክ) ፣

ቅኔ መዝረፍ ፣

የተዘረፈውን ቅኔ ማስቀጸል/ፍቺ ፣ርቃቄ ፣ሙያ/

ቅኔ ማስነገር/ማረም ፣

ቅኔ ያወቁትን በቤተ ክርስቲያን ማስቀኘት ፣

#### ለ. የተማሪው ድርሻ

ግስ ማጥናት ፣

የተዘረፈውን ቅኔ መቀጸል (ማጥናት)

ቅኔ ቈጥሮ መንገር ፣

የታረመለትን ቅኔ መቀጸል (ማጥናት)

እነዚኽ ነገሮች ተማሪው ቅኔ ለመቍጠር ያግዙታል ። ግሶችን ማጥናት ፣ ነባር ስሞችን ማጥናትና የተዘረፉ ቅኔዎችን በትኩረት ማጥናት የቅኔ ትምህርትን ቀላል ከሚያደርጉ ኹኔታዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

## የቅኔ ቅጸላ (ጥናት) ኺደት

፩. ንባብ/ዘር ፡- የቅኔውን ንባብ ሸምድዶ መያዝ ፣

፪. ፍቺ ፡- በንባብ የተሸመደደውን ቅኔ መፍታት ፣

፫. ርቃቄ ፡- የቅኔውን ሠምና ወርቅ ለይቶ ማመስጠር ፣

ሠም ፡- የቅኔውን ሠማዊ መልእክትን ማብራራት ፣

ወርቅ ፡-የቅኔውን ወርቃዊ መልእክት ማብራራት ፣

፬. የቅኔው ሕብረ ቃል ፡- ሠምና ወርቁን አንድ ያደረገውን ቃል መመርመር

፭. ሙያ ፡- በቅኔው ውስጥ ያሉ አገባቦችን ፣ ስሞችን ፣ ግሶችን…አገልግሎታቸውን ማወቅ ፣

፮. የቅኔው ዋና መልእክት ፡- የቅኔው ሃይማኖታዊ ፣ ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊ መልእክትን መገንዘብ

፯. የቅኔው መንገድ ፡- የቅኔውን መንገድ ስያሜ ማውጣት ፣

፰. የቅኔው ዘይቤ ፡- የቅኔውን የዘይቤ ዐይነት መለየት ፣

## የቅኔ ትምህርቶች

- ☞ ቅኔ ዘረፋ ፣ቅኔነገራ ፣ቅኔ ቅጸላ
- ☞ የቅኔ ምራታ ፣የቅኔ ፍች
- ☞ የቅኔ ርቃቄ ፣ የቅኔ ሠምና ወርቅ
- ☞ የቅኔ ሙያ ፣ግስ ገሰሳ
- ☞ ግስ ርባታ ፣ነባር አንቀጽ ርባታ
- ☞ ታሪክ ትረካ ፣አገባብ ቅጸላ ፣ግስ ቅጸላ
- ☞ ነባር ቅጸላ ፣ቅኔ ኀዳና
- ☞ ርባታ ቅጸላ ፣ዜማ ልክ ፣ ገቢር ተገብሮ ወዘተ ናቸው ።

## ፬. ባሕረ ሐሳብ/ዘመን አቈጣጠር

ባሕረ ሐሳብ መሠረቱ ቅዱሳት መጻሕፍት ሲኾኑ ከጥንት ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት የነበሩ ምሁራን ስለ ጠፈር ምርምር ፣ ስለ ሥነ ፈለክ ምርምር ዐየረ ዐየራትን ወጥተው ስለ ሕዋ ሲመራመሩበት የነበረ አኹንም ድረስ በርካታ ሊቃውንት የሚመራመሩበት ጥልቅ ምስጢር ያለው ትምህርት ነው

**ከባሕረ ሐሳብ ጥቅሞች ጥቂቶችን ስናይ**

- ዓመተ ዓለምን ለማወቅ
- ወንበርን ፣ አበቅቴን እና መጥቅዕን ለማወቅ
- የዕለታትን ፣ የአጽዋማትን ፣ የበዐላትን ወዘተ ተውሳኮች ለማወቅ
- ዓመተ ዓለምን ለመስፈር ለመቀመር
- ዘመናትን ለመስፈር
- የበዐላትን ዕለታት ለመለየት
- በአሕዛብ ሀገር ጾምን ለመጠበቅ
- የበዐላትን ዕለት በሥርዓት ለመጠበቅ
- የቤተ ክርስቲያንን ዕውቀት ለመረዳት
- በዐላትን ቁጥሮች ለመረዳት አእምሮን ለማስፋት
- ያለ አጋዥ መሳሪያ ጊዜን ለማወቅ ይጠቅማል

ስለኾነም ጳውሎስ ኦንላይን ቅኔ ቤት ስለ ባሕረ ሐሳብ ትምህርት ሰፊ ዕቅድ ነድፎ በማስተማር ላይ ይገኛል ።

**ባሕረ ሐሳብ/ዘመን አቈጣጠር ትምህርቶች**

- ወንጌላውያን
- መጥቅዕና አበቅቴ
- መደብና ወንበር
- መባጃ ሐመርና ተውሳክ
- የአጽዋማትና በዓላት አወጣጥ
- ኢየአርግና ኢይወርድ

- **ሠርቃት/አሥርቆት**
- **የብርሃናትና ነፋሳት አፈጣጠር**
- **ኬክሮስና ኬንትሮስ**
- **ዓመተ ሰማዕታት ወዘተ ናቸው ።**